# ዶሮና ቀባሪ

(ወለላዬ ከስዊድን - welelaye2@yahoo.com)

## ዶሮ

ወዳጄ እንደምነህ - ውዱ ጎረቤቴ
ባለህበት ቦታ - ይድረስህ መልዕክቴ

የልጄ ሠርግና - የሟች ልጅህ ቀብር
አንድ ላይ መሆኑ - ፈጥሮብኛል ችግር

መቼም ይገባሃል - ግልጽ ነው ነገሩ
ብዙ ነው ማዕረጉ - የሠርገኛ ክብሩ

ስለዚህ አደራ - የልጄን ታላቅ ሠርግ
በደስታ በሆታ - እንዳሳልፍ በወግ

በዛ ቀን ተነስተህ - ልጅህን ስትቀብር
ሰዎችን ሰብስበህ - አታብዛ ግርግር

እንደውም ጨርሶ - ከሞት ላታድናት
በሳቅ በደስታ - በ`ልልታ ቅበራት

ለለቅሶኛው ሁሉ - ይኼን ንገርልኝ
ነገ ማታ ድረስ - መልስህን ላክልኝ

## ቀባሪ

ክቡር አስተዳደር - የላኩልኝ መልዕክት
እጅግ አስገራሚ - ድንቅ ነው በእውነት

ታስራ ተገንዛ - ልጅ ልትቀበር
ተሞሽረች አሉኝ - የርስዎ ልትዳር

ለክብርዎ ሲባል - ለርስዎ ወግ ማዕረግ
እንድስቅ አዘዋል - ለቅሶዬን በመንፈግ

እንደዚህ አድርጎ - ቀኑ ከከበደ
በርስዎ አስተዳደር - ታምር ከወረደ

ኀዘንና ደስታ - መውጣቱ መውረዱ
አንድ ስለሆነ - ሁለቱም መንገዱ

መቼም ምን ይደረግ - በእልልታ ልቅበራት
እርስዎም ልጅዎን - በለቅሶ ይዳሯት

ወይም ደስታ ኀዘን - እንዳይቀያየጥ
ስምምነት አ'ርገን - ቤት እንለዋወጥ

እግረ - መንገዱንም - በዚህ - አዲስ መንገድ
መከራን ይቅመሱ - እኔም ደስታ ልልመድ

Design by EZ